# ጥናት አንድ ቆላስይስ 1፡1-14

የጥናት ዓላማ፡ በህይወታችን ብዙ እግዚአብሄር ደስ የሚሰኝባቸው ፍሬዎችን ማየታችን ከግባችን ደረስን ማለት እንዳልሆነ በመረዳት ዘወትር ከፊታችን ያለውን ለመያዝ እጃችን መዘርጋት እንዳለበት ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምሮ እግዚአብሄር የፈቃዱን እውቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ ይሞላባችሁ ዘንድ ስለእናንተ መጸለይና መለመን አላቋረጥንም፡፡›› ቆላ 1፡9

1. ቆላ 1፡1-14 በአንድነት ይነበብ፡፡ ለቆላስይስ ሰዎች ሰላምታ የሚቀርብላቸው ከማን ነው? ጳውሎስ ራሱን ምን በማለት ነው ያስተዋወቀው? ለተጻፈላቸው ሰዎች የሰጣቸውን ሶስት መጠሪያዎች ተናገር፡፡
2. በቁ3 ላይ ስታነብ የሚጸልየው ሰው ማን ነው? 1ኛ ቆሮ1፡4፣ ኤፌ1፡16፣ ፊሊ1፡4 ላይ ያሉት ጸሎቶች በዚህ ክፍል ከሚደረገው ጸሎት የሚጸልየውን ሰው በተመለከተ የሚለየው በምን መንገድ ነው? ሁለቱን አጻላለዮች በማየት መማር የምንችለው ነገር ምንድነው?
3. በቁ4-5 ላይ የምሥጋናው ምክንያት ሆነው የቀረቡትን ሁለት ነገሮች ተናገር፡፡ ለእነዚህ ነገሮች ምንጭ ሆኖ የተጠቀሰው ነገር ምንድነው?
4. ቁ6-8ትን ስታነብ በውስጣቸው ያለው ተስፋ ፍሬ ማፍራትና ማደግ ስለጀመረበት ስለጀመረበት ጊዜ ምን ይናገራል? ወደዚህ መረዳት እንዲመጡ የረዳቸውና ወንጌልን ለመስማት ምክንያት የሆናቸው ሰው ማን ነው?
5. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ስለ ኤጳፍራ የምታያቸውን ባህርያት ዘርዝር፡፡ ለአንድ የእግዚአብሄር አገልጋይ እነዚህ ባህርያት ምን ያህል አስፈላጊ ናቸው ትላለህ? አስረዳ፡፡
6. በቁ9 ላይ የምናየው የጸሎት አይነት በቁ3 ከምናየው የሚለየው እንዴት ነው? እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ለሞላባቸው ሰዎች ተጨማሪ የጸሎት ርዕስ መገኘቱ ስለራስህ ህይወት ምን ይነግርሃል?
7. በቁ10-12 ላይ ለጌታ እንደሚገባ መኖርንና በሁሉ ደስ ማሰኘት የሚለውን ለማስረዳት የዘረዘራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
8. ወደፊት ልትደርስበት የምትናፍቀውና በህይወትህ እንዲገለጥ በጸሎት የምትተጋለት መንፈሳዊ ፍሬ አለ ወይ? ባሉበት መርካት ጤናማ ስላልሆነ ዘወትር እጆቻችን ሌላ ለመጨበጥ የተዘረጉ እንዲሆኑ ጌታ ይርዳን!

# ጥናት ሁለት ቆላስይስ 1፡15-29

የጥናት ዓላማ፡ ፍጥረትን ሁሉ ከመፍጠሩም አልፎ ዓለም ተያይዞ እንዲቆም ያደረገው ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ከቁጥጥር ውጭ የወጣ መስሎ የሚመስለንን የእኛንም ሁኔታ አጽንቶ ሊያቆም የሚችል አምላክ እንዳለን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው፡፡‹‹ ቆላ 1፡17

1. ቆላ 1፡15-29 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ክፍል እርሱ እያለ የሚናገረው ስለማን ነው? በእርሱ ተፈጠሩ የሚላቸውን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ አልተጠቃለለም የምትለው ነገር ካለ ተናገር፡፡
2. በቁ15 ላይ ‹‹አምሳል›› ወይም “Image” የሚለው ቃል እንዴት ትረዳዋለህ? ‹‹ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው፡፡›› ሲል ክርስቶስ ፍጡር ነው ማለቱ ነው ወይስ ምን ለማለት ፈልጎ ነው? አስረዳ፡፡
3. በእርሱና በቤተ ክርስትያን መሃል ስላለው ግንኙነት ቁ18 ምን ይናገራል? ክርስቶስ የቤተ ክርስትያን ራስ ነው የሚለውን ሃሳብ እንዴት ነው የምትረዳው?
4. ጳውሎስ በቁ 18-20 ላይ አካል የሚለውን ሃሳብ በተጠቀመበት አጠቃቀምና በሮሜ 12፡4-8 ላይ በተጠቀመበት አጠቃቀም ላይ ምን ልዩነት ታያለህ?
5. በአንተ አመለካከት በቆላ 1፡15-20 ባለው ክፍል ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ግልጽ በሆነ መንገድ ይናገራል የምትለውን አንድ አረፍተነገር ወይም ቃል ተናገር ብትባል የትኛውን ትላለህ?
6. ቁ21-22 ያለው ክፍል የሚናገረው ስለማን ነው? በእነዚህ ሰዎች ህይወት ውስጥ ስለተከናወነው ለውጥ ይህ ክፍል የሚናገራቸውን ሃሳቦች በዝርዝር ተወያዩባቸው፡፡
7. በቁ24-26 ላይ ጳውሎስ ለቤተ ክርስትያን እያደረገ ስላለው አስተዋጽዖ የሚናገራቸውን ሁለት ሃሳቦች ተናገር፡፡ በዚሁ ክፍል ደግሞ ቃሉን በተመለከተ የተጻፉ ሁለት ሃሳቦችን ዘርዝር፡፡
8. ቁ28-29ስን በማንበብ ጳውሎስ በወንጌል አገልግሎቱ ግብ አድርጎ የሚለፋለት ነገር ምንድነው? ከዚህ ግብ ለመድረስ የሚጠቀምባቸው መንገዶች ምን ምንድናቸው? በ1ኛ ቆሮ 3፡9 ላይ ያለውን እውነት ይህ ክፍል እንዴት እንደሚያጎላው አስረዳ፡፡
9. ወደ ቁ17 ላይ በመመለስ ‹‹ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው›› ሲል ምን ትረዳለህ? የእርሱ ሁሉን ነገር ከመፍጠር አልፎ ሁሉም ተያይዞ በሥርዓት ጸንቶ እንዲኖር ማድረጉ ምን ዋስትና ይሰጥሃል? ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ነገር ባቀደው መንገድ ስለሚጨርሰው ምን ይሆን ይሆን የሚለው ሃሳብ ሊያስጨንቀን አይገባም፡፡

# <u>ጥናት ሶስት ቆላስይስ 2፡1-12</u>

የጥናት ዓላማ፡ ክርስትያኖች አንዳችን ለሌላችን ልንተጋና ልንጋደል የሚያስፈልን ዋነኛ ነገር  የእግዚአብሄር ምሥጢር የሆነውን የጥበብና የእውቀት ሁሉ ማደሪያ ክርስቶስን እንደሚገባ እንድናውቀው መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ፍጹም የሆነውን የመረዳት ብልጥግና አግኝተው የእግዚአብሄር ምሥጢር የሆነውን ክርስቶስን እንዲያውቁ እተጋለሁ፤ የተሰወረ የጥበብና የእውቀት ሃብት ሁሉ የሚገኘው በእርሱ ዘንድ ነውና፡፡›› ቆላ 2፡2-3

1. ቆላ 2፡1-12 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ የቆላስይስ አማኞች እንዲያውቁ እንዲያውቁት የፈለገው ነገር ምን ነበረ? ሐዋርያው ተጋድሎውን የተጋደልኩት ለማን ስል ነው ይላል?
2. በዚህ ክፍል ውስጥ ‹‹እጋደላለሁ›› ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ ቃልስ የሚያካትተው ምን ምን ይመስልሃል?
3. ቁ1-5ትን በማንበብ ጳውሎስ ለተጋድሎው የሚሰጣቸው ምክንያቶች ምንድናቸው? ክፍሉን ስናነብ ሐዋርያው እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን እንደሚገባ እንዲያውቁት ስለፈለገበት ምክንያት ምን እንረዳለን?
4. እነዚህ አማኞች የተሰወረ የጥበብና የእውቀት ሃብት ሁሉ የሚገኘው በክርስቶስ ውስጥ መሆኑን ማወቃቸው የሚጠቅማቸው ምክንያት ሆኖ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው አንድ ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል የሀሰተኞቹ ትምህርት ምን እንደሆነ ሳያስተምራቸው እውነቱ ምን እንደሆነ ነው የነገራቸው፡፡ ከዚህ ምን መማር ይቻላል?
5. ቁ5 ስለቆላስይስ ሰዎች ህይወት የሚነግረንን ሁለት ሃሳቦች ተናገር፡፡ ከነዚህ ሁለት ሃሳቦች በመነሳት እነዚህ አማኞች መልካም የክርስትና ህይወት ምስክርነት አላቸው ማለት የሚቻለው ለምንድነው?
6. ቁ6-7ት ውስጥ አማኞች እንዲያደርጉ የሚጠየቁትን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡
7. በቁ8-12 ባለው ክፍል ውስጥ አማኞች በክርስቶስ ስለሆነላቸው ነገር የተነገሩትን ቢያንስ አምስት ነገሮች ዘርዝር፡፡
8. በተራ ቁ2 ላይ የተጠየቀውን ጥያቄ አስመልክቶ፤ የእግዚአብሄር ምሥጢር የሆነውን ክርስቶስን በሚገባ እንድናውቀው አንዳችን ለሌላችን መጋደል የሚኖርብን ዋነኛ ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ክርስቶስን እንድናውቅ ከማበረታታት ይልቅ ሌላ ትኩረት የሚሰጠው ነገር ታያለህ ወይ? ለምን? ዛሬ ከተማርከው ተነስተህ በህይወትህ ልታደርግ ወይም ልትለውጥ ያለህ ነገር ካለ ለወገኖች አካፍል፡፡

# ጥናት አራት ቆላስይስ 2፡13-23

የጥናት ዓላማ፡ የራሳችንንም ሆነ የሌሎችን ሰዎች መንፈሳዊነት የምንለካው በክርስቶስ በሆነልን ውስጣዊ ለውጥ እንጂ በወጭ በሚታይ ወይም ሰው ሰራሽ ሥርዓቶችን በመከተልና ባለመከተል መሆን እንደሌለበት ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንግዲህ በምትበሉትም ሆነ በምትጠጡት ወይም በዓልን፣ ወር መባቻንና ሰንበትን በማክበር ነገር ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ ናቸውና፤ አካሉ ግን ክርስቶስ ነው፡፡›› ቆላ 2፡16-17

1. ቆላ 2፡13-23 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ13-15 ቀድሞ ሙታን ስለሆንበት ሁኔታ የሚሰጠን ምክንያት ምንድነው? ይህንኑ ክፍል ስናነብ እግዚአብሄር ለዚህ ችግራችን መፍትሄ አድርጎ የተጠቀመበት ነገር ምን ነበረ ይላል?
2. ከላይ በተመለከትናቸው ቁጥሮች ውስጥ እኛን ካለንበት ሁኔታ ውስጥ ለማውጣት እግዚአብሄር ክርስቶስ አማካኝነት ያከናወናቸውን ነገሮች በሙሉ ዘርዝር፡፡
3. በቁ16ትን ሲጀምር ‹‹እንግዲህ›› በሚለው ቃል ነው፡፡ ይህ ቃል ቁ16-17 ላይ ያለውን ሃሳብና በቁ15-15 ያለውን ሃሳብ እንዴት ያያይዛል ብለህ ታምናለህ? ይህንን አስመልክቶ የጳውሎስ ማጠቃለያ ሃሳብ ምንድነው?
4. የመላዕክት አምልኮ አጉል ትህትና ተደርጎ ሊታይ የቻለበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ? ይህስ አመለካከት በእግዚአብሄር አመለካከት አጉል ሆኖ የሚታየው ለምን ይመስልሃል?
5. በቁ18-19 ላይ ያለውን ሰው የሚገልጡት ቢያንስ ሶስት ነገሮችን ተናገር፡፡ ‹‹ራስ ከሆነው ጋራ ግንኙነት የለውም፡፡›› ያለበት ምክንያት ለምንድነው?
6. የቁ20-23 ዋነኛ ትኩረት በምን ላይ ነው? ሐዋርያው በዚህ ክፍል ሊያስተምራቸው የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ ምንድነው?
7. ቁ23 ላይ እነዚህ ነገሮች በውስጣችን ሊፈጥሩ ይችላሉ የሚላቸው ሶስቱ ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህ ነገሮች በህይወታችን ማድረግ ስለማይችሉት አንድ ነገር ይህ ክፍል ምን ይላል?
8. ወደ ቁ16-17 ተመልሰን ስንመለከት በአሁኑ ዘመን የሰዎችን መንፈሳዊነት ስንለካ የምንገኝባቸውን ነገሮች ተናገር፡፡ የሰዎችን መንፈሳዊነት በዚህ መንገድ መለካት አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው ትላለህ? በክርስቶስ ባለህ ነገር እንጂ የሰውን ህግ በመጠበቅና ባለመጠበቅ ላይ ጊዜህን ማጥፋት እንደማያስፈልግህ እወቅ፡፡

# ጥናት አምስት ቆላስይስ 3፡1-11

የጥናት ዓላማ፡ ልባችን ትክክለኛውን ነገር መሻቱና አዕምሯችንም ትክክለኛውን ነገር ማሰቡ በመንፈሳዊ እድገታችን ላይ እጅግ ትልቅ የሆነ አስተዋጽዖ እንዳላቸው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሄር ቀኝ በተቀመጠበት በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤ ሃሳባችሁም በላይ ባለው ላይ እንጂ በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን፡፡›› ቆላ 3፡1-2

1. ቆላ 3፡1-11 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ላይ የቆላስይስ ሰዎች እንዲያደርጉ የሚነግራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነዚህን ነገሮች ማድረግ የሚኖርባቸው ለምንድነው ይላል?
2. ቆ2፡13 ላይ እንደሞትን በሚናገረው ሃሳብና በዚህ በ3፡3 ላይ በሚናገረው ሞት መሃል ያለውን ልዩነት አስረዳ፡፡
3. እንደገና ሞትን አስመልክቶ 3፡3 ‹‹ሞታችኋል›› ሲለን 3፡5 ደግሞ ‹‹ግደሉ›› ይለናል፡፡ እነዚህ ሁለት ክፍሎች ይቃረናሉ ወይ? ካልሆነ እንዴት እንደምትረዳቸው ተናገር፡፡
4. በእነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ ክርስቶስ የሚለው ስም ስንት ጊዜ ተጠቅሷል? የተጠቀሰውስ ከምን ጋራ ተያይዞ ነው? የዚህ ስም ከምንባቡ ውስጥ መውጣት ምን ሊያስከትል ለውጥ ያመጣል ትላለህ?
5. ቁ5-11 እንደገና ይነበብ፡፡ ቁ6 ላይ የሚናገረው የእግዚአብሄር ቁጣ የሚመጣበት ምክንያት ለምንድነው? ይህ ቁጣ እንዳይመጣስ መፍትሄ አድርጎ ሐዋርያው ያቀረበው ሃሳብ ምንድነው?
6. ቁ5 ላይ ‹‹ስለዚህ›› በማለት ቁ1-4 እና 5-11 የሰፈሩት ሃሳቦች ያገናኛል፡፡ በምን መንገድ ነው የእነዚህ ሁለት ክፍሎች ሃሳብ ይያያዛል ብለህ የምታምነው?
7. ከሃጥያት ወጥቶ በጽድቅ መኖርን አስመልክቶ ይህ ክፍል የተጠቀመበት ምሳሌያዊ አነጋገር ምን እንደሆነ ተናገር? ለምን ይመስልሃል ጳውሎስ አውልቃችሁ ስላስቀመጣችሁት ከሚለው አነጋገር ይልቅ ‹‹አውልቃችሁ ስለጣላችሁት›› የሚለውን አባባል የመረጠው?
8. በቆላ 3፡10 እና በሮሜ 8፡29 መካከል ምን ተመሳሳይ ሃሳብ ይታይሃል? 3፡11ን በዚህ አንጻር ስትመለከተው ምን ለማለት እንደፈለገ ትረዳዋለህ?
9. በቁ1-4 ያለው ሃሳብ በቁ5-11 ለምናነበው ነገር በምን መንገድ መሰረታዊ ነው ብለህ ብላል ትላለህ? የልብህን መሻትና የአዕምሮህ አስተሳሰብ ለእድገትህ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ምን ያህል ተረድተሃል? ሰማያዊውን ነገር መሻትና ሰማያዊውን ነገር ማሰብ ለመንፈሳዊ እድገት ወሳኝነት ስላለው ዘወትር፤ መሻቴ ምንድነው? በአዕምሮዬስ የሞላው ነገር ምንድነው ብለህ መጠየቅን አትርሳ፡፡

# ጥናት ስድስት ቆላስይስ 3፡12፡17

የጥናት ዓላማ፡ ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን ወገኖቻችንን ለመምከር፣ ለማስተማርም ሆነ ወይም በዝማሬ ለማገልገል ካስፈለገ የእግዚአብሄር ቃል ሙላት በህይወታችን ውስጥ መኖሩ ወሳኝ መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹የክርስቶስ ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ ተማማሩ፤ ተመካከሩ፤በመዝሙርና በማህሌት፤በመንፈሳዊም ቅኔ በማመስገን በልባችሁ ለእግዚአብሄር ዘምሩ፡፡››ቆላ 3፡16

1. ቆላ 3፡12-17 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ12 ላይ የቆላስይስ ሰዎች እንዲለብሱ የሚጠየቋቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? በቁ10 ላይ ‹‹ለብሳችኋል›› ተብሎ ተነግሯቸው ለምንድነው በዚህ ክፍል ቁ12 ላይ እንደገና ‹‹ልበሱ›› የሚላቸው?
2. ስለ እነዚህ አማኞች ማንነት በተመለከተ ቁ12-14 ምን ይናገራል? እነዚህ አባባሎች ከእግዚአብሄር ጋራ ስላለን ግንኙነት ምን ይነግሩሃል?
3. ‹‹ልበሱ›› የሚለውን አነጋገር ስትሰማ ልብስን አስመልክቶ ቀድሞ ወደ ሃሳብህ የሚመጣው ሃሳብ ምንድነው? የተናገርከውን ሃሳብ የተለያዩ ባህርያትን ከመልበስ ጋራ በማዛመድ ያለውን ግንኙነት ተናገር፡፡
4. ‹‹እርስ በእርስ ተቻቻሉ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. በቁ12-14 ላይ ከተዘረዘሩት ባህርያት መካከል በህይወትህ ለመለማመድ ከባድ ሆኖ ያገኘኸው የትኛውን ነው? በክርስትያኖች መካከል ለመለማመድ ስንቸገር የምታያቸው ውስጥ ሁለቱን ባህርያት ተናገር፡፡ ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኛው ቢኖረን ብዙውን ነገር ያቀላል ትላለህ?
6. ቁ14 ፍቅር እንዴትና በምን መንገድ ነው ሁሉን በፍጹም አንድነት ሊያስተሳስር የሚችለው? ሌላውን ሁሉ ለብሰን ፍቅርን ባንለብስ የሚያጎድለው ነገር ምን ይመስልሃል?
7. እያንዳንዱ አማኝ በቆላ 3፡15 እና በኤፌ 4፡3 ላይ የታዘዘውን ትዕዛዝ ቢፈጽም በቤተ ክርስትያን ውስጥ ምን ለውጥ ሊያስከትል ይችል ይመስልሃል ወይ? ይህ ማለት ሰላምን ለመጠበቅ ሰዎች ሲስቱም ዝም ብሎ ማለፍንም ያጠቃልላል ማለት ነው ወይ?
8. በቁ16 ላይ አማኞች ምን እንዲያደርጉ ነው የታዘዙት? በነዚህ በታዘዟቸው  ነገሮች ውስጥ ቃሉ ምን ዓይነት ሥፍራ ነው የተሰጠው?
9. በዘመናችን ከምንማራቸው ትምህርቶች፣ ከምንመከራቸው ምክሮችና ከሚወጡት ዝማሬዎች በክርስቶስ ቃል ሙላት አንጻር ሲመዘኑ ከ1-10 ብትሰጥ ስንት ትሰጣቸዋለህ? ተወያዩበት፡፡ አንተስ በምክርህ፣ በትምህርት  ወይም በዝማሬህ ለእግዚአብሄር ቃል ምን ያህል ቦታ ሰጥተኸዋል? ራስህንም ሆነ ሌሎችን ለማገልገል የቃሉ በውስጥህ በሙላት ማደር አስፈልጊነቱን አውቀህ ትጋ፡፡

# ጥናት ሰባት ቆላስይስ 3፡18-4፡1

የጥናት ዓላማ፡ ሥልጣን ሁሉ ከእግዚአብሄር ስለሚሰጥ፤ የሰዎቹን ማንነት ተመልክተን ሳይሆን ሥልጣኑን በላያቸው ያኖረውን ጌታ በማየት ለተቀበሉት ሥልጣን የመገዛት ግዴታ እንዳለብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ማንኛውም ሰው በሥልጣን ላሉት ሹማምት መገዛት ይገባዋል፤ከእግዚአብሄር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣናት በእግዚአብሄር የተሾሙ ናቸው፡፡›› ሮሜ 13፡1

1. ቆላ 3፡18-4፡1 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ ለሚስቶች የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው? ይህንን ማድረግ የሚኖርባቸው ለምንድነው?
2. በዚሁ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ለባሎች ያስተላለፈው ትዕዘዝ ምን ነበረ? መራራ አትሁኑባቸው ሲል ምን ማለቱ ይመስልሃል?
3. ልጆችስ በዚህ ክፍል የታዘዙት ትዕዛዝ ምንድነው? መታዘዝ ስለሚኖርባቸው ምክንያት ምን ተናግሯል? ይህ ምክንያት በዚህ ስፍራ ለመታዘዝ የተሰጣቸው ምክንያት እኛ ለሰማያዊ አባታችን ስለምንታዘዝበትስ ሁኔታ ምን ያስተምረናል?
4. አባቶች ልጆቻቸውን በተመለከተስ ምን ታዘዋል? የታዘዙትን ትዕዛዝ አለመፈጸም የሚያስከትለው ነገር ምንድነው? በመማረርና ተስፋ በመቁረጥ መሃል ሊኖር የሚችለው ግንኙነት ምን እንደሆነ አስረዳ፡፡
5. በቁ22 መሰረት ሰው ሊያገለግል ወይም ሥራውን ሊሰራ የሚችልባቸው የተጠቀሱት ሁለት ዓይነት መንገዶች ምንና ምንድናቸው? አማኝ የሆነ ሰው መከተል የሚኖርበት መንገድ የትኛውን ነው?
6. ቁ24-25 ደግሞ አማኞች ለአለቆቻቸው/ለጌቶቻቸው ለምን ጌታን እንደሚያገለግሉ ሆነው መስራት እንደሚኖርባቸው የሚናገራቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው?
7. ቁ24‹‹የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስን ነው፡፡›› በሚለው መሰረት አንድ አማኝ ሙሉ ቀን የግንበኛነት ስራውን ሰርቶ በመግባት የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ነኝ ቢል ምን ይሰማሃል? የዚህን ሰው አገልግሎት ‹‹የሙሉ ጊዜ አገልጋይ›› ብለን ከምንጠራው ጋራ እንዴት ሊነጻጸር እንደሚችል ተናገር፡፡
8. ለጌታቶች/ለአሰሪዎች የተሰጠው ትዕዛዝስ በ4፡1 ላይ ምንድነው? የተሰጠው ምክንያትስ ምንድነው?
9. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሄር የሥልጣን ተዋረድ ያደረገባቸው ስንት ድርጅቶች ታያለህ? በዚህ ምንባብ ውስጥ የምናያቸው በየትኞቹ ውስጥ ይጠቃለላሉ? ከእነዚህ ውስጥ በየትኛዎቹ ውስጥ ራስህን ታገኘዋህ? ለመታዘዝ የትኛው ያዳግትሃል? ዓለም ከሚሰጠው አመለካከት ቢለይም ሰው ከሚለው ይልቅ እግዚአብሄርን ልንሰማ ይገባናል፡፡

# ጥናት ስምንት ቆላስይስ 4፡2-18

የጥናት ዓላማ፡ እንደ በርናባስ የሚሸከምና የሚያበረታታ ሰው ካለ ዛሬ ለእግዚአብሄር ሥራ አይጠቅሙም ተብለው የሚታሰቡ ሰዎች ነገ በእግዚአብሄር ጸጋ ጠቃሚ ሰዎች እንዲሆኑ ማብቃት እንደሚቻል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ጳውሎስ ግን እርሱን ይዞ ለመሄድ አልፈለገም፤ ምክንያቱም ቀደም ሲል ማርቆስ ከእነርሱ ተለይቶ…አብሯቸው ስላልሄደ ነበር፡፡›› ሥራ 15፡38

‹‹ማርቆስ በአገልግሎቴ ስለሚረዳኝ ከአንተ ጋራ ይዘኸው ና፡፡›› 2ኛ ጢሞ 4፡11

1. ቆላ 4፡2-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ2-4 ዋና ትኩረት ያደረገበት ርዕስ ምንድነው ትላለህ? ቁ2ትን ብቻ በማንበብ ስለጸሎቱ ዓይነት ምን ትረዳለህ?
2. በቁ3 ላይ የቆላስይስ ሰዎች እንዲጸልዩ የሚጠየቁት ስለማን ነው? የተሰጣቸው የጸሎት ርዕሶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ጳውሎስና ጓደኞቹ ለአገልግሎታቸው የጸሎት ጥያቄ ማቅረብ ለኛ ምን ያስተምረናል?
3. ቁ5 እና ቁ6 ዋና ትኩረት ያደረገው በማን ላይ ነው? እነዚህ ቁጥሮች በምን መንገድ ነው የክርስትናን ህይወት ሁለቱን ዘርፎች የሚነኩት? አስረዳ፡፡
4. በቁ7-9 ላይ የምናያቸው ሁለት ሰዎች ማንና ማን ናቸው? ስለ እነዚህ ሰዎች የተነገሩት የጋራ የሆኑ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
5. ቁ12-13 የሚናገረው ስለማን ነው? ይህ ክፍል ስለዚህ ሰው ምን ይነግረናል? ኤጳፍራ ለቆላስይስ ሰዎች በጸሎት የሚጋደልባቸው ሶስት ርዕሶች ምን ምንድናቸው?
6. ቁ16ትን ስታነብ አንድ የምታስተውለው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ ቁ17 ላይ ለአግሪጳ ከተነገረው ነገር ለራስህ ምን ትማራለህ?
7. ወደ ቁ10 ተመልሰን ስንመለከት ስለማርቆስ ምን ይነግረናል? የሐዋርያት ሥራ 12፡25ትን፣ 13፡13ትንና፣ 15፡37-41ድንና 2ጢሞ 4፡11ድን በማንበብ በማርቆስ ህይወት የሆነውን ነገር አስረዳ፡፡ በዚህ ወንድም ህይወት ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋጽዖ አድርጓል የምትለው ሰው ማን ነው?
8. ለእግዚአብሄር አገልግሎት በብዙ ሊጠቅሙ የሚችሉ የነበሩ፤ ነገር ግን ዛሬ በተለያዩ ምክንያቶች ዳር ይዘው የተቀመጡ እነማን ወደ አዕምሮህ ይመጣሉ? ተመልሰው ለፍሬአማነት እንዲበቁ እስከዛሬ ምን እርምጃ ወስደሃል? ጠቃሚ ሰዎች እንዲሆኑ ምናልባትም የሚጠብቁት የአንተ ወይም የእኔ ማበረታታትና አይዞህ ማለት ብቻ ሊሆን ስለሚችል የእምነት እርምጃን ውሰድ፡፡